## ምድብ አንድ (የሙዓለ ሕፃናት ተማሪዎች)
## 14 ኛ ሳምንት

# ቀይ ባሕርን መሻገር

**ዓላማ**

❖ እግዚአብሔር በቀይ ባህር የሠራውን ተዓምር መማር፣

**ምንባብ**

❖ ዘጸ 5 እና 7-11

**መግቢያ**

❖ እግዚአብሔር ለሙሴ የተናገረውን ታስታውሳላችሁ? ያለፈው ሳምንት ትምህርታችሁን ከመምህር ጋር ከልሱ። ዛሬ ሙሴ እግዚአብሔር እንዳዘዘው ወደ ግብፅ ሄደ በብዙ ተዓምራት ነፃ ካወጣቸው በኋላ በመንገድ ላይ የተደረገላቸውን የመጀመሪያ ተዓምራት እንማራለን።

**ትምህርቱ**

❖ ሙሴ ወደ ግብፅ ተመልሦ ፈርኦን ህዝቡን እንዲለቅ ሲነግረው፤ ንጉሡ አልተቀበለውም። እግዚአብሔር በብዙ ተዓምራትና ቅጣት ፈርኦንና ሕዝቡን ከቀጣ በኋላ ግን ፈርኦን ነፃነቱን ፈቀደ። ሙሴ እና የእግዚአብሔር ሕዝብ ባሕረ ኤርትራ ሲደርሱ ግን ፈርኦን ሃሳቡን ቀየረ፤ እስራኤልን ወደ ግብፅ የሚመልስ ሠራዊት ላከ። ሕዝቡም ይሄን ሲያዩ በሙሴ ላይ አለቀሱ።

❖ እግዚአብሔርም ሙሴ በያዘው በትር ቀይ ባህርን እንዲመታ አዘዘው። ሙሴ ይሄን ሲያደርግም የቀይ ባህር ውሃ ለሁለት ተከፈለ። በመሐልም ደረቅ መሬት ታየ። እስራኤልም በቀይ ባህር መሐል በደረቅ መሬት ተሻገሩ።

❖ ፈርኦንና ሠራዊቱም እስራኤልን ተከትለው ወደ መሐል ገቡ። እስራኤል ወጥተው ሲጨርሱ እና ፈርኦንና ሠራዊቱ መሐል እያሉ ሙሴ መልሶ ባህሩን በበትር መታው። ባህሩም ወደ ደረቀው መሬት ተመለሰ። የፈርኦን ሠራዊት በሙሉ፣ ፈረሶቻቸው እና ሰረገላዎቹም በቀይ ባህር ሠጠሙ።

**ሙከራ፣**

1. ፈርኦን እስራኤልን እንዲወጡ የፈቀደው በመጀመሪያ ነው?

ሀ. አዎ ለ. አይደለም

2. ፈርኦን እንዲሄዱ የፈቀደላቸው መቼ ነው?

ሀ.ሙሴ ሲያዘው ነው ለ. እግዚአብሔር ብዙ መከራዎችን ከሰደደ በኋላ ሐ. እንዲሄዱ አልፈቀደላቸውም

3. የፈርኦን ሠራዊት ከእሰራኤል በኋላ ሲመጣ እግዚአብሔር ሙሴን ምን አድርግ አለው?

ሀ. ተመልሦ እንዲዋጋ ለ. ወደ ግብፅ እንዲመለሱ ሐ. በተከፈለው ባህር መሐል በደረቀ መሬት

**ተግባር፣**

1. ከጀርባ ያለው ሥዕል በቀለም/ከለር/አስውቡት
2. የሚከተለውን መዝሙር ከመምህር ጋር ተለማመዱና ዘምሩ

| **መዝሙር** | **ትርጉም** |
|---|---|
| ንሴብሖ (2) ለእግዚአብሔር | እናመስግነው (2) እግዚአብሔርን |
| ስቡሓ ዘተሰብሐ | ምሥጉን ነው የተመሠገነ |



ይቆየን፡፡